## የግል ወገናዊ ጥሪ፤

ከ አያል ሰው ደሴ፦ *“የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሸንጎ” ..... (ክፍል አራት፣ ከክፍል ሦስት የቀጠለ)*

### ለ) መሠረታዊ የአስተሣሰብ ለውጥ ላይ የተመሠረተ አዲስ የፖለቲካ ቅኝት መያዝ፤

ከዚኽ በላይ በ“ሀ” እንደተጠቀሰው የሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ቁንጮዎች ምንም ዓይነት ብሔራዊ የኃላፊነት ስሜት በጎደለው አስተሣሰብና አካሄድ በሥልጣን ላይ ለመቆየት ሲሉ ብቻ የሚከተሏቸው አሉታዊነት የበዛባቸው፣ በጣም መዘዘኛና ጦሰኛ መርኃ-እቅዶች (ፖሊሲዎች) ከሌሎች ጋር በመዳመር አገራችንንና ሕዝቧን ሊፈነዳ ለደረሰ ዙሪያ-ጥምጥም አደገኛ የውጥረት ሁኔታ መዳረጋቸው ግልጥ ነው። ከተፈጠረው የአስተማማኝ ብሔራዊ አማራጭ ክፍተት አኳያ ደግሞ ይኽ ውጥርጥር ያለና በማንኛውም ጊዜ ሊፈነዳ የደረሰ ፈታኝ ሁኔታ ሕዝባችንን ዞሮ-ዞሮ ማንም ተጠቃሚ ወደማይሆንበትና በፀፀት ወደማይመለስ አጠቃላይ ቀውስ፣ ትርምስና በአብዛኛው ጎሠኝነትን መሠረት ላደረገ የርስ-በርስ እልቂት (ጀኖሣይድ) የሚወስድ አደገኛ ደረጃ ላይ መድረሱ ብዙዎችን ስጋትን ላይ ጥሏል። ይኽ ያንዣበበ አደጋ ከመድረሱ በፊት ተረባርቦ ማስወገዱ የማንኛውም ኢትዮጵያዊ የጋራ ኃላፊነት ነው። አንዳንድ ወገኖች ይኽ ሁሉንም ሊያሣስብና እረፍት ሊነሣ የሚገባ ግልጥ ስጋት በተለመደው የተመሰከረለትና አኩሪ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጨዋነትና አስተዋይነት እውን ላይሆን ይችላል የሚል እምነት አሁንም አላቸው።

በኢትዮጵያ ሕዝብ የረቀቀ ጨዋነት፣ ትዕግስትና አስተዋይነት ከፍተኛና የማይናወጥ እምነት ያለኝ ሰው ነኝ። ሆኖም በአሁኑ የአገራችን የመስክ ላይ ሁኔታ ይኽንን በላያችን ላይ ያንዣበበና በሁሉም መሥፈርት የአገርን ኅልውና አጥብቆ የሚፈታተንና ወደ-ዘግናኝ ጎሠኛ ትርምስ ሊወስድ የሚችል ስጋት በሕዝባችን የተመሰከረለት ጨዋነትና ብልኅነት ብቻ ሊወገድ አይችልም ባይ ነኝ። ለዚያ ደግሞ ምክንያቶቹ በአንድ በኩል ለእነዚኽ ብርቅዬ እሴቶች ምንጭና መሠረት የሆኑት ብሔራዊ ማንነት፣ ኢትዮጵያዊ ክብርና የዜግነት ትሥሥር ሆን-ተብሎ በሂደት መቦርቦራቸው፣ በሌላ በኩል የችግሩ መጠን፣ ስፋትና ጥልቀት ካለው የኃይል አሠላለፍና ከሚታዩ ልዩ-ልዩ የውጭ አሉታዊ ተፅዕኖዎች አኳያ በአሁኑ ጊዜ ይኽ ውስብስብ ችግር በማንኛውም ኅብረተሰብ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ሰው ጤነኛ አስተሣሰብ ላይ የሚያሣድረው በቀላሉ ከቁጥጥር ውጭ የሚሆን የሰው አውሬኣዊ ባኅሪ አንገቱን ቀና ሊያደርግና የበላይነት እንዲኖረው የሚያደርግ ምሬት-ወለድ ክስተትን የሚያስከትል ሁኔታ በመመቻቸቱ ነው። ለዚኽ ደግሞ ዋነኛ ተጠያቂው የአገዛዙ ቁንጮዎች የሚከተሉት መሠሪያዊ የአድልዖ ፖለቲካ፣ በሥልጣን ላይ ለመቆየት ሲሉ እየተጠቀሙበት ያለውና አጠቃላይ የአገሪቱን የፖለቲካ ሕይዎት እንዲገዛ የተደረገው፣ ሌላውም እስካሁን በተከተለውና በሁሉም ረገድ ገዥነት እንዲኖረው የፈቀድንለት ፖለቲካዊ-ጎሠኛ/ጎጠኝነት ርዕዮት ነው። ስለሆነም ስለ-ዴሞክራሲም ሆነ ሌላ ጉዳይ ላይ ከመንጠላጠላችን በፊት ይኽን ሰዎችን በእኩል ዓይን የማያይ፣ ያለ-ጠላት ኅልውና የሌለው፣ የልዩነት አጥር-አጣሪ፣ ኋላ-ቀርና ትንሽ-አስተሣሰብ ላይ የቆመ አደገኛ ፍልሥፍና ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን መሠረት ባደረገ አዲስ አስተሣሰብና የፖለቲካ ቅኝት መተካቱ ይዋል-ይደር የማይባል ጉዳይ ነው እላለሁ። እዚኽ ላይ *መሠረታዊ ለውጥ ለማድረግ ድፍረቱና ቁርጠኝነቱ ከሌለን አደጋን ሆን-ብለን እየጎተትን እንደሆነ፣* **ሁሉም ተጠቃሚ የሚሆንበት የሥርዓት ለውጥ የሚባል ነገርም እንደማይኖር ግልጥ ይሁን።**

ከምንም በላይ ሕዝብንና አገርን ባስቀደመ መንፈስ፣ ሕዝብን አክብሮርና የሕዝብን ኃያልነት አምኖ መከበርንና ተኣማኒነትን የዋጀ፣ ኢትዮጵያዊ አንድነቱን የጠበቀና ታግሎ የሚያታግል ሁነኛ ብሔራዊ አማራጭ እስከሌለ ድረስ የተከፈተ በር ሲያገኝ የማይገባ ቀማኛ፣ ሰነፍ ሲያገኝ የማይጎብዝ ደካማ የለምና በልዩነታችን ክፍተት እየተጠቀሙ አገራዊ ፍቅርና ብሔራዊ ስሜት የሌላቸውና አገራቸውን በቁም የሚሸጡ የሕወሓት/ ኢሕአዴግ አምባ-ገነን ቁንጮዎች በሕዝብ ላይ ሊፈነጩ መቻላቸው ሊገርም ከቶ አይችልም። የፖለቲካ ቅያሱንም (አጀንዳውን) እንዲቆጣጠር በመደረጉ፤ አወቅነውም አላወቅነው፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፤ አገዛዙ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ገላውን-ሰድዶ እንደፈለገው እንዲጋልብ ፈቅደንለታል። በአንድ መልኩ ይሁን በሌላ እነሱም ቢወገዱም እንኳ እነሱ የቆሙበትን ከፋፋይና ኋላ-ቀር ፖለቲካዊ-ጎሠኝነት/ጎጠኝነት ፍልሥፍና ከፖለቲካ ቅኝታችን ጨርሶ ካላስወገድን በስተቀር እንዲኹ ቢያንስ ሕዝብ በጥቂቶች ጨቋኝና አድልዖኣዊ የአገዛዝ ሥርዓት ሥር ላለመውደቁ፣ አልፎም ሕዝባችንን ለዘግናኝ የርስ-በርስ ትርምስ ላለመዳረጉ ዋስትና አይኖርም። ስለሆነም የአገር-ወዳድና ዴሞክራት ኢትዮጵያውያን ቀጣዩ ሰልፍ ይኽንን ያገናዘበ፣ በአዲስ አስተሣሰብ ላይ የቆመ የፖለቲካ ቅኝት ሊይዝና የጨዋታ ሕጉንም የቀየረ ሊሆን ይገባል።

በመሠረቱ በፖለቲካዊ-ጎሠኝነት/ጎጠኝነትም ይሁን በዘርና በሐይማኖት ላይ መሠረቱን የጣለ ፖለቲካዊ ቅኝት/እምነት ልዩነትን ዋነኛ መነሻና መድረሻ ያደረገ ፍልሥፍናና የፖለቲካ ቅኝት

በመሆኑ በኅብረተሰቡ ውስጥ የነበሩና ያሉ ልዩነቶችን የሚያጠብና አንድነትን የሚያስገኝ ሣይሆን ያሉትን ይበልጥ የሚያሠፋና የሚያደነድን፣ አዳዲሶችንም የሚፈለፍል አስተሣሰብ ነው፡፡ በመሆኑም ይኸ ዓይነት አሠላለፍና ጉዞ መፋታትን ዓላማና ግቡ ያደረገ ጋብቻ ዓይነት ከንቱ የጎን-ለጎን ጉዞ ይሆናል፡፡ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች የሚከተሏቸው የጥፋት ፖሊሲዎችና የሚያሣዩአቸው ኢ-ዴሞክራሲያዊ፣ ወገንተኛና አድልዖአዊ ባኅሪያት፣ አፈናና ጭቆና ሁሉ የሚመነጩት ደግሞ ከሌላ ሣይሆን ከሚከተሉት ፖለቲካዊ-የጎሠኝነት/ጎጠኝነት ፍልሥፍናና ከያዙት የዓብዮታዊ ዴሞክራሲ ርዕዮት መሆኑ ሊታወቅ የሚገባው ይመስለኛል፡፡ በነ-አቶ መለስ ሕወሓት የጠላነው ፖለቲካዊ-ጎሠኝነት/ጎጠኛነት ከአገዛዙ ጋር ችግር አለን ስላሉ ብቻ በሌሎቹ ላይ እንዴት መልካም ሆኖ እንደሚገኝ ጨርሶ ሊገባኝ አይችልም፡፡

አዎን ይኸ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን መሠረት ያደረገ የፖለቲካ ቅኝት ሲነሣ ሁሉን ነገር በፖለቲካዊ-ጎሠኝነት/ጎጠኝነት መነፅር ማየትን የግድ በሚል አስተሣሰብ ለሚመሩ ወገኖች "መብታቸውን" ለመደፍጠጥ የታሰበ ተደርጎ እንደሚቀርብ እረዳለሁ፡፡ ይኸ ሥነ-ልቦናዊ ተፅዕኖ ደግሞ ኢትዮጵያውያን በተለይም ጎሠኛ ልሂቃን ከአምሣ ዓመታት በላይ የተከተሉት "በወል መብት" ስም የተጠቀለለ ነጠላ የፖለቲካ ቅኝት ጋር የተያያዘና እየሰመመ የሄደ አስተሣሰብ የወለደው እንደሆነ ብዙ አከራካሪ አይመስለኝም፡፡ ተወደደም-ተጠላ እንደ-ኢትዮጵያ ላለ ስብጥሩ የበዛ ኅብረተሰብ ደግሞ ለሁሉም የአገሪቱ ዜጎች ፍትኅንና እኩልነትን የሚያረጋግጥ ሥርዓት በልዩነት ላይ በቆመ "አንድነት" ሣይሆን በአገራዊ አንድነት ሥር በሚስተናገድ ልዩነት ብቻ ነው እውን መሆን የሚችለው፡፡ ስለሆነም፣ ከዚኽ መነሻውም-መድረሻውም ልዩነት ከሆነ ፖለቲካዊ-ገሠኝነት/ገጠኝነት አስተሣሰብ መላቀቁ ለአሁኑም ሆነ በተለይም ከቀጣይ ትውልዶች ዘለቄታዊ ጥቅም መከበር፣ ከአስተማማኝ ሰላም፣ ከፍትኅና እኩልነት መረጋገጥ፣ ከኅብረተሰብ እድገት፣ ከአገር ልማትና ብልፅግና አኳያ አማራጭ የሌለው ጉዳይ እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል፡፡ የኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት እምነት ደግሞ የመተሣሰብ፣ የመከባበር፣ የፍትኅ፣ የእኩልነትና የነፃነት፣ የአንድነት፣ የአልበገሬነት፣ የብሔራዊ ክብርና ኩራት፣ የጋራ ማንነት እሴቶች ምንጭና መገለጫ እንደሆነ ግልጥ ይሁን፡፡

አገሪቷንና ሕዝቧን ለመታደግ በቀጠለው መራር ትግል ድርጅቶች የተቻላቸውን የተናጠል ጥረት አላደረጉም ማለት አይደለም፡፡ የተጠየቁትን ሁሉ መስዋዕትነት ለመክፈል ዓይናቸውን የማያሹና ይኸንንም በተግባር ያስመሰከሩ፣ አሁንም ትዳራቸውም ሕይዎታቸውም ሁሉ ለዚኹ አገራዊና ሕዝባዊ የተቀደሰ ዓላማ የሆነ፣ በአገራቸውና በሕዝባቸው ፍቅር የተቃጠሉ፣ በጎ የሚመኙ ቆራጥ ታጋዮች በየድርጅቱ ሞልተዋል፡፡ ለሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች አቅምና ጉልበት በመሆን ቀጥ አድርጎ ያቆማቸው በጠንካራ አገራዊና ሕዝባዊ መርኅ ላይ የቆመ የተባበረ ኃይልን ሊያግዱና ሊገቱ የማይችሉት የአፈና መረቦቻቸውና የተረጋገጠ አረመኔአዊ ባኅሪያቸው ሣይሆን በውስጥ አተካሮና አለመተማመን የተበከለው እና እራሱን ሣይለውጥ ለውጥ-ፈላጊ የሆነው ኃይል እንደሆነ ግልጥ ሊሆን ይገባል፡፡ የዚኽ ምንጩ ደግሞ ጨርሶ እውን መሆን በማይችል ምናባዊ ጠባብ የቡድን ጥቅም ጥንውትና አገርንና ሕዝብን ማስቀደም ካለመቻል የሚደረግ ስንጥር ጉዞና ትንሽ አስተሣሰብ የወለደው የፖለቲካዊ-ጎሠኝነት/ጎጠኝነት አባዜ ይመስለኛል፡፡ ከዚኽ አባዜ መውጣት ደግሞ ለሁሉም ጠቀሜታ የሚኖረው አዎንታዊ ለውጥ እንዲመጣ ለምንፈልግ ወገኖች ሁሉ መነሻችን ሊሆን ይገባል፡፡

**ሐ) በአዲስ አደረጃጀት ሁነኛ ብሔራዊ አማራጭ መፍጠር፤**

የሚደረገው ሕዝባዊ ትግል አዎንታዊ ውጤት-አስመዝጋቢ እንዲሆን የኃይል አሠላለፉ ቀደም-ሲል ከተደረጉ የጋራ ጥረቶች በቂ ትምሕርት የቀሰመ፣ እንዲለወጥ የሚፈለገውን ኃይል ባኅሪ በቅጡ ያገናዘበ፣ ለውጡ ለምን ዓላማና ግብ እንደሆነ በማያሻማ ሁኔታ ግልጥ ያደረገ፣ አደረጃጀቱና አሠላለፉም ላለው ሁኔታ መጣኝ ብቻ ሣይሆን ከሕወሓት/ኢሕአዴግ ማዶ ያዬ ሊሆን ይገባል፡፡ ባልተቀየረ ሥነ-ልቦናና እስካሁን ተይዞ በቆየ የተዛባ የፖለቲካ ቅኝት ላይ የተመሠረተ አደረጃጀትና የኃይል አሠላለፍ ተይዞ፣ ባልተለወጠ የጨዋታ ሕግና በተመሣሣይ ተጫዋቾች አዲስ ድርጅትም ሆነ የድርጅቶች ስብስብ መፍጠሩ አንድም የተተለመው ግብና ግቡን ለመጨበጥ የሚያስችለው የትግል ዘዴ (ታክቲክና ስትራቴጂ) ተለውጧል፣ አለበለዚያም እንዲለወጥ የሚፈለገው ኃይል (ሥርዓት) ተፈጥሮአዊ ባኅሪውን ቀይሯል ማለት ይሆናል፡፡ ያ ሣይሆን በቆየ አስተሣሰብና አዘቦታዊ አደረጃጀት ለመቀጠልና የተለዬ ውጤት መጠበቅ ግን የጤና አይሆንም፡፡ ድኅረ-ምርጫ-ዘጠና-ሰባት ያለው የመስክ ሁኔታ የሚያረጋግጠው ደግሞ አገዛዙ አፈናውንና እመቃውን ይበልጥ ያጧጧፈበት፣ የስለላ መረቡን በቤተሰብ ደረጃ ሣይቀር የዘረጋበትና የቁጥጥር ሽምቀቆውን በእያንዳንዱ ዜጋ አንገት ላይ ለማስገባት የሚረባረብበት፣ "አውራ-ፓርቲነቱን" በይፋ አውጆ "ሕጋዊ-ፈቃድ" ያልቸው ድርጅቶች መሠረታዊና መደበኛ የሚባሉ ድርጅታዊ ተግባሮችን ለማከናዎን የማይችሉበት ትብታቦ ውስጥ

የሚገኙበት በመሆኑ ማንም ክፍል ምንም ዓይነት ትብብር ለመፍጠር ከመከጀሉና ሕዝብን ዳግም ተስፋ-አጨላሚ አዙሪት ውስጥ ከማስገባት በፊት ሁኔታውን ከቡድንና ከድርጅት ሣይሆን ከአገርና ከሕዝብ ዘለቄታዊ ጥቅም አኳያ ሊመረምር ይገባል እላለሁ፡፡

ሕዝባችን አመኔታውን የሚጥልበት ሁነኛ አገራዊ አማራጭ ባለመኖሩ ለሥርዓት ለውጥ በሚያደርገው ትግል የሚያስመዘግባቸውን ድሎች ለማስከበርም ሆነ እንዲሁም ጥረቱ ቢሣካ በልዩ-ልዩ አሉታዊ ኃይሎች ትግሉ ተጠልፎ አገራችን ወደ-አፍራሽ አቅጣጫ እንዳታመራና “ከድጡ-ወደ-ማጡ” እንዳይኬድ ብዙዎች የምንሰጋበትና የምንጨነቅበት ጉዳይ እንደሆነ መገመቱ አያዳግትም፡፡ ይኸ ስጋትም ሕዝባችን በግፈኞች ላይ ተባብሮ እንዳይነሣና የተረገጡ መብቶቹን እንዳያስከብር ዋነኛ እንቅፋት እንደሆነበት አጠራጣሪ አይመስለኝም፡፡ ስለሆነም ይኸንን ሁሉን-አቀፍ አገራዊ አካል በማቋቋም በአገራችን የተፈጠረውን አደገኛ የሁነኛ አማራጭ ክፍተት መሙላት ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል እላለሁ፡፡ ለአዎንታዊ ለውጥ የቆመ ሁሉ ከእንግዲኽ የሚያደርገው ሠልፍ በአስተሣሰብም ሆነ በአደረጃጀቱ አንድ ሁነኛ ብሔራዊ አማራጭ ሆኖ ለመቅረብ የሚያስችለው ሊሆን ይገባል፡፡ አስተሣሰቡና አደረጃጀቱም ከፖለቲካዊ-ጎሠኝነት/ጎጠኝነት ቅኝት የተላቀቀና ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ብቻ ማዕከል ያደረገ መሆን አለበት፡፡

መቼም እስከ-አሁን ተቃዋሚው የለውጥ ኃይል በተጓዘበት የአደረጃጀት ዘይቤና አሠላለፍ በአገራችን ለተፈጠረው የሁነኛ ብሔራዊ አማራጭ አደገኛ ክፍተት ምላሽ-ሰጭ ለመሆን የሚያስችለው እንዳልሆነ ግልጥ ነው፡፡ የዚኽ ሰንክ ዋናው ተጠያቂ ደግሞ ከተከተልነው አጠቃላይ የፖለቲካ ቅኝት በተጨማሪ ይኽንኑ አካል የሚመሠርቱት አባል ድርጅቶች ናቸው፡፡ እያንዳንዱ መሥራች (አባል) ድርጅት ወደ ጋራ ስብስብ ሲመጣ በድርጅት ነፃነት ስም ሁሉም ጣራና ግድግዳውን እንደያዘ እና ዓላማውም እያንዳንዱ ከአጠቃላዩ የሚያገኘውን “ጥቅም” ተቀዳሚ አድርጎ ነው፡፡ በመሠረቱ እያንዳንዱ ድርጅት በተፈጠረበት መልክ እንዲፈጠር የሆነበት የየራሱ ምክንያት አለው፡፡ የሚታገለውም ዓላማዬና ግቤ ብሎ ለያዘው እምነት ነው፡፡ ይኽ ግልጥ ነው፡፡ እያንዳንዱ የጋራው ስብስብ አባል ሲሆን ድርጅቱ ከጋራ ስብስቡ የሚያገኘው “ጥቅም” ላይ ያተኮረ መሆኑ አዲስ ነገር ሆኖ ላይገኝ ይችላል፡፡ ሆኖም፣ ያ አግባብነት የሚኖረው ዴሞክራሲያዊ እሴቶች በተደላደሉበትና ድርጅታዊ ነፃነት በተከበረበት፣ እያንዳንዱ ድርጅት በተናጠል “መብቴ” የሚለውን ማስጠበቅ የሚችልበት ሁኔታ ሲኖር ነው፡፡ በአሁኑ የአገራችን ሁኔታ የሚደረገው ትግል ግን ወርዶ-ወርዶ የጋራ ኅልውናን ለማስጠበቅ የሚደረግ መሆኑ በተገቢ ግልጥ ሊሆን ይገባል፡፡ ስለሆነም በአሁኑ የአገሪቱ የመስክ ላይ ሁኔታ በሚቋቋሙ ስብስቦች አማካይነትም ሆነ በተናጠል ይኽ  ነው የሚባል ማስጠበቅ የሚቻል የተናጠል “ድርጅታዊ ጥቅም” አለ ማለት አይቻልም፡፡

በጥንቃቄ ከታዬ እስካሁን የቆዩ ስብስቦች ያረጋገጡት የግለሰቦችን ስምና ከፋፋይ ጎሠኛ/ጎጠኛ አመለካከቶችን ማስቀጠል መቻላቸው ብቻ ይሆናል፡፡ እስካሁን ባለው ልምድ ድርጅቶች በጋራ ስምምነት በሚፈጥሯቸው ስብስቦች ውስጥ አባል መሆን ለአንዳንድ በተናጠል መቆም ለማይችሉ ድርጅቶች ኅልውና በጣም አስፈላጊና በአገዛዙ ተነጥሎ ከመመታትና ጨርሶ ከመክሰም ለመዳን ስለሚረዳ መጠለያና መደበቂያ ዋሻ በመሆን ሊያገለግላቸው እንደቻለ አከራካሪ አይመስለኝም፡፡ ያ ግን ለአጠቃላዩ የሚያስገኘው ጥቅምም ሆነ የሕዝቡን ትግል በአዎንታዊ መልኩ ወደ-ፊት በማራመዱ ረገድ ይኸ ነው የሚባል አስተዋፅዖ ይኖረዋል ብሎ መገመቱ ስህተት ይመስለኛል፡፡

“የድርጅት ጥቅም ማስጠበቅ” የሚል ጥያቄ በአሁኑ የአገራችን ሁኔታ ቅንጦት ይመስለኛል፡፡ ወቅቱ ደግሞ የቅንጦት እንዳልሆነ ግልጥ ነው፡፡ አለ የሚሉ ካሉ ግልጥ ቢያደርጉት ደስ ይለኛል፡፡ እንደኔ-እንደኔ የጋራ ኅልውናችን ላይ አደጋ ባንዣበበበት በአሁኑ የአገራችን ፈታኝ ሁኔታ በተለይ ለአገር አንድነትና ለዴሞክራሲ ቆሚያለሁ ከሚል ማንኛውም ወገን “የድርጅት ጥቅም” ይከበር የሚል ጥያቄ ማቀንቀኑና መንገታገቱ በሚሰጥም መርከብ ውስጥ ሆነው በመቀመጫ ወንበር የሚጣሉ ሰካራሞችን ከመሆን ለይቶ ማየት ይቸግረኛል፡፡ በአምባ-ገነን አገዛዝ፣ በአሉታዊ ኃይሎችና በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ማዕበል እየተናጠችና እየተናወጠች ያለችውን የጋራ አገር ኅልውና ማረጋገጡ የቅድሚያ-ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ ሌላው ሁሉ የጋራ ኅልውናንና የዜጎችን መብቶችና ሰብኣዊ ክብር ካረጋገጥን በኋላ የሚመጣ ይሆናል፡፡

እስካሁን ድረስ ያለ መሠረታዊ የአስተሣሰብ ለውጥ በድርጅት ላይ ድርጅት፣ በኅብረት ላይ ሌላ ኅብረት ሲቋቋም አይተናል፡፡ ሕወሓት/ኢሕአዴግ ሥልጣን ከጨበጠ ጊዜ አንስቶ የተቋቋሙ ድርጅቶችን ቆም-ብሎ አንድ-በ-አንድ ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ የትኛው ድርጅት ነው እድገቱ በአስተማማኝ የቀጠለ? ስንቶቹ ድርጅቶች ናቸው በታላቅ ጉጉትና በከፍተኛ ተስፋ ተመሥርተው፣ በአንድ ጊዜ ተመንድገው እድገታቸው በአጭር-ጊዜ ተቀጭቶ እየሟሸሹ፣ እየጠወለጉና እየከሰሙ የሄዱት? ስንቶችስ ናቸው የጋራ ስብስብ ውስጥ በመግባት ድርጅታቸው ውስጣዊ እድገትን ማግኘት ባይችልም ቢያንስ 'ሊቀ-መንበር' በሚባለው ግለሰብ አማካይነት እንበለ-አባላት የድርጅታቸውን ባዶ ስም ተሸክመው የቆዩና በድርጅት መብት ስም የጋራውን ትግል ቀይደው የያዙ? በአገር ውስጥም

“ምርጫ” የሚሉት የአገዛዙ ቧልት በመጣ ቁጥር ሌሎችን “በኔ ክልል አትግቡብኝ” የሚል “የጎልውና” ማስጠበቂያና የሌላቸውን የተፈላጊነት ካርድ የሚመዙት? ያስ ለአጠቃላይ ሕዝባዊ ትግሉ፣ በተለይም ሕዝብ ከፋፋይ የሆነውን መርዘኛ ፖለቲካዊ-የጎሠኝነት/ጎጠኝነት አጥር በመንቀሉ ረገድ በአሉታዊ ገፅታው ካልሆነ በስተቀር ጠቀሜታው ምንድን ነው? የዚያ ዓይነት አካሄድስ ለሕዝባችን ሁነኛ ብሔራዊ አማራጭ እንዳይኖር አስተዋፅዖ አላደረገም ወይ? በመስክ ላይ ያለው የፖለቲካችን ሃቅ ይኸ ነው።

የሥልጣኑ ባለቤት ለመሆንና መብቶቹን ለማስከበር መስዋዕትነት ከመክፈል ቦዝኖ የማያውቀው የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚኽ አደገኛ ክፍተት ባለበት የአገሪቱ ሁኔታና ባለው የኃይል አሠላለፍ የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ከፍሎ አገዛዙን መቀየር ቢችልም እንኳን፤ ያ በራሱ የታገለለትን ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ሊያረጋግጥለትም ሆነ በላዩ ላይ ያንዣበበውን ለአጠቃላይ ትርምስ የመዳረግ ሠፊ ዕድል የማስቀረት ዋስትና ሊሆነው አይችልም። ስለሆነም ለውጥ-ፈላጊው አገር-ወዳድና ዴሞክራት ወገን የሌሎችን የጥፋት አጀንዳ አሟይ ከመሆንም ሆነ ተበትኖ በተናጠል ከመቆም፣ ተስፋ ከመቁረጥም ሆነ እራሱን አቅመ-ቢስ አድርጎ ከማየት አባዜ ሊላቀቅና በራሱ ላይ ቆራጥ የአስተሣሰብ ለውጥ በማድረግ የተፈጠረውን አደገኛ ክፍተት ለመድፈን ጊዜ ሣይወስድ መንቀሣቀስ ይገባል እላለሁ።

ዴሞክራሲያዊ የአንድነት ኃይል የሥርዓት ለውጥ ግቡን ለመጨበጥ እንዲችል እራሱን በኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት መንፈስ በአዲስ መልክ አደራጅቶ ሁነኛ ብሔራዊ አማራጭ ሆኖ እንዲገኝ ማድረግ የሚኖርበት የሚከተሉትን ዓበይት አገራዊ ተልዕኮዎችና ኃላፊነቶችን ለማከናወን ነው።

- ተስፋን በሚያቀጭጭና በሚያሣዝን ሁኔታ የተበተነውና ስብጥርጥሩ የወጣው ለአዎንታዊ ለውጥ የሚታገለው ኃይል በአሁኑ አደረጃጀቱ፣ አካሄዱም ሆነ አሠራሩ ለአገዛዙ ዕድሜ-ቀጥል ከመሆን ውጭ የተፈለገውን ውጤት ሊያመጣ ስለማይችል ይኸንን አስተባብሮና አሰባስቦ ሕዝባዊ ትግሉን ፈር በማስያዝ ባለ ብዙ ዘርፍ ትግሉ ትኩረቱን ባልለቀቀና አቅጣጫውን ባልሣተ ሁኔታ ሕዝብን ማዕከል አድርጎ እንዲቀጥል፣ ማስቻል (ማድረግ)፤
- ይኸንን አደገኛ ክፍተት በመድፈን ሕወሓት/ኢሕአዴግ በሥልጣን ላይ ካልቀጠለ የአገሪቱ አንድነት ሌላ ባለቤት ስለሌለው የመፍረስ አደጋ አለ በሚል በአገዛዙ መሪዎችና በአቀንቃኞቹ የሚደርገው አሣሣች ማደናገሪያ ፍሬ-ቢስ መሆኑን በተግባር በመሻር ለሕዝባችን አለኝታና ሁነኛ አማራጭ ሆኖ መገኘት፤
- በዚኽ ሂደት ቢያንስ በሕዝባችን ላይ እየደረሰ ያለ እንግልት፣ ሰቆቃና ግፍ እንዲቆም፣ የአገዛዙ ቁንጮዎች በራሣቸው ፈቃድና ውሳኔ ብቻ የፈለጉትን ማድረግንና አገርንም ሕዝብንም እንደ ግል ንብረት በመቁጠር ዜጎችን እያፈናቀሉ መሬትን ለባዕዳን የመቸርቸርም ይሁን ዳር-ድንበርን ማስደፈርና ለባዕዳን አሣልፎ የመስጠትን፣ የአገሪቱንና የሕዝቧን መፃዒ-ዕድል በእጅጉ የሚጎዱ እርምጃዎችንና አገርን በቁም እየገደሉ ያሉ ፖሊሲዎችን ቆም-ብለው እንዲያስቡና ገታ እንዲያደርጉ ተጨባጭና ተግባራዊ የሚሆን ጫና ማሣደር፤
- የለውጥ-ፈላጊው ትግል የአገዛዙን ስህተቶችና ጎፀዖች ማጋለጥ ላይ ብቻ የሚወሰን ሣይሆን ለአገዛዙ ሁነኛ አማራጭ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብም አስተማማኝ አለኝታ በመሆን ለሕዝባችን ተጋባራዊ የሚሆኑና ተዓማኒነት ያላቸው ተለዋጭ የመታገያ አማራጮችን በድፍረት በማቅረብ የአገዛዙን የጥፋት ሂደት በብቃት መጋፈጥና ማስቆም፤ በተግባር ላይ ሊውሉ የሚችሉ አማራጮቹንም በተጨባጭ ለሕዝብ ማድረስ፤
- ተከብሮ ሊደመጥ የሚችልና ለአገርና ለሕዝብ ተሰሚ ድምፅና አለኝታ ሊሆንና በሁሉም ረገድና በማንኛውም አገራዊ፣ አካባቢያዊም ሆነ ዓለም-አቀፋዊ መድረኮች እንደ <u>ተለዋጭ መንግሥት</u> ከአገዛዙ በአቻነት ሊቆም የሚችል ሁነኛና አሣማኝ አማራጭ ኃይል መሆን፤
- እነኝኽን በማድረግ በአገራችን ያንዣበበውን የጎልውና ማጣት አደጋ ስጋት በማስወገድ ኢትዮጵያችን ድኅረ-ሕወሓት/ኢሕአዴግ ያላስፈላጊ ትርምስ ሣይኖር በአገራዊ እርቅና ሰላም ሂደት ሕዝባችንን ወደ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት የሚወስድ የሰከነ ሰላማዊ ሽግግር እንዲደረግ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ከወዲኹ ዋስትና መሆን፤ ይሆናል።

ይኸ አካሄድ ደግሞ እስካሁን በትግሉ ቀጥተኛ ተሣትፎ ለሚያደርገው የኅብረተሰብ ክፍል ብቻ ሣይሆን በሕወሓት/ኢሕአዴግ ሥር የሚገኙ ወገኖችንም በተለይ በአገር መከላከያና ፀጥታ ኃይሎች እንዲሁም በየመሥሪያ-ቤቱ (በቢሮክራሲው) ውስጥ ላሉት ለውጥ-ፈላጊ ወገኖች ሁሉ አበረታች፣ ለወደፊቱም ያላስፈላጊ ስጋት የወለዳቸው ማመንታቶችን የሚያስወግድና ትግሉ በነሱ ላይ የመጣ ሣይሆን ለእነሱም እንደሆነ ተስፋ የሚሰጣቸው፣ መተማመኛ የሚሆናቸውና ባመቻቸው መንገድ ሁሉ የትግሉ አካል መሆን እንዲችሉ ዕድል የሚሰጥ እንደሚሆን መገመት ይቻላል።

ለመብቶቹ መከበር በልዩ-ልዩ ጊዜዎች ከዳር-እስከ-ዳር እንደ-አንድ ሰው በጋራ እየተነሣ በየጊዜው አይከፍሉ መስዋዕትነት የከፈለውና መስዋዕትነት ከመክፈል ያልተቆጠበው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በከፈለው መራር መስዋዕትነት ያስመዘገባቸውን ድሎች ሊያስከብርለትና ሊያስጠብቅለት የሚችል ኃይል አለመኖሩና የከፈለውን መስዋዕትነት የሚመጥን ውጤት አለማግኘቱ የቅርብ ጊዜ መራር ተመክሮው ላይ በአገሪቱ ያለው አመኔታውን የሚጥልበት ሁነኛ አማራጭ ካለመኖሩ ክፍተት ጋር ተደማምሮ ያሣደረበት ስጋት እያንዳንዱን ቀጣይ እርምጃ በጥሞናና በጥንቃቄ መመዘን መምረጡ አስገራሚ ሊሆን አይችልም። የኢትዮጵያ ሕዝብ በሰሜን-አፍሪቃና በመካከለኛው-ምሥራቅ እንደታየውና እንደሚታየው ከዳር-እስከ-ዳር እንደ-አንድ ሰው በጋራ መነሣትና ግፈኛ አምባ-ገነኖችን አስወግዶ መብቶቹን እንዳያስከብር እክል የሆነበት ይኸው የሁነኛ ብሔራዊ አማራጭ ኃይል ክፍተት እንደሆነ እምነቴ ነው። በአገሪቱ ለተፈጠረው አደገኛ ክፍተት አስተማማኝ መፍትሔ ሣይሰጥ ሕዝብን ተነስ ብሎ መቀስቀሱ የተፈለገውን ሰሚ ማግኘቱ ሊያጠያይቅ ቢችልም፣ አድራጎቱ ግን እጅግ ኃላፊነት የጎደለው ነው።

ክቡራትና ክቡራን ውድ ኢትዮጵያውያን፤

በአገዛዙ ላይ አስገዳጅነት ያለው ትግል ለማድረግም ሆነ በዚያ አስገዳጅነት የሚገኝን የሕዝብ ድል ማስከበር፣ አገዛዙንም በሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መተካት፣ ሕዝብ ሰላሙን፣ አገርም መረጋጋቱን ማረጋገጥ የሚቻለው ደግሞ አገራዊ አንድነታችን ሲጠበቅ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። <u>ከማንኛውም ጊዜ ይበልጥ የአገር አንድነት ጥያቄ ለምንም ይሁን ለምን በሁለተኛ ደረጃ የሚቀመጥ ጉዳይ እንዳልሆነ ለሁሉም ግልጥ ሊሆን ይገባል።</u> የምንታገልለት ፍትኅ፣ እኩልነትና ዴሞክራሲ እውን መሆን የሚችሉት ሰላምና መረጋጋት ሲኖሩ ብቻ ነው። እነኝኸ እሴቶች መረጋገጥ የሚችሉት ደግሞ መከራና ፈተና የበዛበትና በሁሉም አቅጣጫ እየተገዘገዘ ያለው አንድነታችን ሲከበር ብቻ በመሆኑ የሚደረገው ትግል ይኸንን መሠረት የሚያረጋግጥ ሊሆን ይገባል። ከአጠቃላዩ ሕዝብ ጥቅም ይበልጥ ለተወሰነ ጠባብ ዓላማ የቆሙና የሚታገሉ፣ በተለይም ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን በጠላትነት የፈረጁ፣ ክፍሎች አንድነት የሚሉትን ጣጣ አታንሱ፣ በአሁኑ ጊዜ ትግሉ የዴሞክራሲ ጥያቄ ላይ ብቻ ያተኩርና "ሌላው ከድል በኋላ በሕዝብ የሚወሰን ይሆናል" የሚል ማጃጃያቸውን ሲያቀነቅኑ አንዳንድ ብኩኖችም ይኸንኑ በሌጣው ተቀብለው በማቀንቀንና እንደ ገደል-ማሚቶ እያስተጋቡ በሞኝ አጋፋሪነት አጃቢና አጫፋሪ መሆናቸው በትዝብት እየታየ ነው። እነዚያ ቡድኖች "በኋላ ይወሰናል" የሚለውን ማነሁለያ ይዘው የቀረቡት በአገሪቱ ላይ የተፈጠረውን ክፍተት ከመገንዘብና ሸዓብያ የኤርትራን ሕዝብ "ነፃነት ወይስ ባርነት" የሚል ምርጫ-የለሽ-ምርጫ የተገኘውን ተመክሮ በአዲስ ዙር ለመጠቀም ከማለም መሆኑ ግልጥ ይሁን።

ለረጅም ጊዜ "በወል መብት" ስም ልዩነትን ዋነኛ መሠረቱ ያደረገው የፖለቲካ ቅኝት በዜጎች ላይ ከፍተኛ ሥነ-ልቦናዊ ጫና ያሣደረ በመሆኑ፤ ለትግሬውም፣ ለአማራውም፣ ለኦሮሞውም፣ ለጉራጌውም፣ ለሃድያውም፣ ለአኙዋኩም፣ ለሶማሌውም፣ ለወላይታውም፣ ወዘተ... ለአጠቃላዩ ምልኣተ-ሕዝብ ፍትኅ እንዲሰፍን፣ እኩልነት፣ የሕግ የበላይነትና ሰብዓዊ ክብርና ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን እንዲሆንና የጤንነትና የምግብ ዋስትና እንዲረጋገጥ ለመሣሰሉ የማንኛውም ዜጋ መሠረታዊ ጥያቄዎች የጋራ ምላሽና ሁሉም ተጠቃሚ የሚሆንበት መፍትሔ ለማስገኘት በሚደረገው አገራዊ ትግል ላይ በእጅጉ እንዳጠላበት ሊታወቅ ይገባል።

<u>ይኸ 'ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ብቻ መሠረት ያደረገ' አዲስ ቅኝት ከእንግዲኽ የትግሉን መሥመር በትልቁና በግልጥ በአንድ በኩል ከሕወሓት/ኢሕአዴግ ጀምሮ ያሉትን የዚኽ ርዕዮት አራማጆች በአንድ ቋት ባስቀመጠ፤ በሌላ በኩል የአገራችንን አንድነትና የሕዝባችንን ሉዓላዊነት ቅድሚያ በሰጠ አሠላለፍ የፈረጀ ሊሆን የግድ ይሆናል።</u> ይኸ ደግሞ እውን መሆን የሚችለው ኢትዮጵያን እንደ ጋራ አገራችን፣ የሕዝባችንም ዕድል የማይነጣጠልና በማንኛውም ዜጋ ላይ የሚደርስ በደል የሁሉም፣ የአንዱ ብሶት የሁሉም አድርጎ በመውሰድ፣ የማንም ነፃነትና መብት በሌላው ኪሣራ ሊረጋገጥ እንደማይችል በመረዳት፣ ፍትኅና እኩልነት ለሁሉም መምጣት እንዳለበት፣ ዜጎችን ከዞግ፣ ከጎሣ፣ ከአካባቢ፣ ከጠባብ የድርጅትም ሆነ የቡድን ስሜት፣ ወዘተ. ባለፈ እምነት፣ አስተሣሰብና አመለካከት ላይ የተመሠረተ ሲሆን ብቻ መሆኑ ለሁሉም ግልጥ ሊሆን ይገባል።

በአሁኑ ጊዜ ሕዝባችን እየወረደበት ያለውን ግፍ ለማስቆም፣ ዙሪያ-ጥምጥም ችግሮቹን በዘላቂነት ሊፈታ የሚችልበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ለአዎንታዊ ለውጥ የቆሙ ወገኖች ሁሉ ሕዝብ አመኔታውን ሊጥልበትና አክብሮ ሊከተለው፣ በአገዛዙም ሆነ በሌሎች ሦስተኛ ኃይሎች ተደማጭነትን ሊያስገኝ፣ ሕዝባዊ ትግሉንም በሁሉም ዘርፍ በማዕከልነት የሚመራና ፈር ለማስያዝና ዳር ለማድረስ ቁርጠኝነትና ድርጅታዊ ብቃት ያለው እንቅስቃሴውን በመንግሥት ደረጃ ማካሄድ የሚችል የፖለቲካ ድርጅቶችን፣ ልዩ-ልዩ የሲቪክና የሙያ ማኅበራትን፣ ምሑራንና የአገር

ሽማግሌዎችን፣ በአጠቃላይ አገር-ወዳድና ዴሞክራት ወገኖችን ሁሉ ያቀፈ “የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሸንጎ” ለሕዝባችንና ለአገራችን በሁነኛ አማራጭነት በአስቸኳይ እንዲቋቋም ወገናዊ ጥሪየን በታላቅ አክብሮት አቀርባለሁ።

ይኸ በሁሉም ኢትዮጳያንና ሕዝቧን የሚያስቀድሙ ኃይሎች በጋራ መቋቋም አለበት የምለው “የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሸንጎ” እስካሁን እንደታየው ለምርጫ ወይም አንድን የተወሰነ ፖሊሲ ለመቃዎም ወይም እንደ “እስረኞች ይፈቱ” ዓይነት ጥያቄን ለማስተጋባት፣ ወዘተ. በተወሰነ ጠባብ አጀንዳ ዙሪያ ለሚደረግ ዓላማ የሚውል ውሱን መሰባሰብ አይደለም። ይኸ በአዲስ አስተሣሰብ ለውጥ ላይና በኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት እምነት ላይ የሚመሠረት አካል ትግሉን ፈር የማስያዝና የአገዛዙን የጥፋት አጀንዳዎች በበቂ የማስቆም፣ አገዛዙን በዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ለመተካት የሚያስችል የሰከነ ሰላማዊ ሽግግር የማድረግ ተልዕኮዎችና ኃላፊነቶች ያሉት ሁሉን-አቀፍ ኃይል መመሥረቱ ይዋል ይደር የማይባል በመሆኑ አዲስ የመሰባሰብ ጥረቶች ሁሉ በዚኹ ላይ ያተኮሩ እንዲሆኑ በትኅትና አጠይቃለሁ። የሕዝባችንን ቀጣይ ሰቆቃ እናስቁም፣ አገራችን ከብተና እናድን ከተባለ የተሻለው መንገድ ይኸ ብቻ ነው። “የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሸንጎ” እንዴት መቋቋም እንደሚችል፣ አደረጃጀቱን፣ አወቃቀሩንና አሠራሩን በተመለከተ የተዘጋጀውን ዝርዝር አሣብ ደረጃ በደረጃ በድርጅቶች የምክክር ጉባዔ ላይ አቀርባለሁ።

በዚኸ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት እምነት ላይ መሠረቱን በጣለ አዲስ የፖለቲካ ቅኝት የምታምኑና የተሰበጣጠረው ታጋይ ክፍል በአንድ ሁሉን-አቀፍ ስብስብ ውስጥ በመካተት “የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሸንጎ” እንዲመሠረትና ትግሉን በኃላፊነት እንዲመራ፣ ለአገራችንና ለሕዝባችንም አስተማማኝ አገራዊ ኃይልና ሁነኛ አማራጭ መኖር እንደሚያስፈልግ የምታምኑ ወገኖች ሁሉ፤

ሀ) በየአካባቢያችሁ በጉዳዩ ላይ ምክክር የሚያደርግ ስብስብ እንድትፈጥሩ፤

ለ) የፖለቲካ ደርጅቶችም ይሁን የሲቪክና የሙያ ስብስቦች አባላትና ደጋፊዎች ድርጅቶቻችሁ በዚኸ የአንድነት መሥመር እንዲሰለፉና ከጅምሩ ተሣታፊ እንዲሆኑ ጥረት እንድታደርጉ፤

ሐ) በተለይ ለአገር አንድነትና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን መሆን የምትታገሉ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች የሆናችሁ ድርጅታችሁ ምንም ያኸል የተቀደሰ ዓላማ ቢኖረው፣ ምን ያኸል ቁርጠኛ አባላት ቢኖሯችሁ እየከፋ ለመጣው የአገራችን ሁኔታና ዘርፈ-ብዙና መጠነ-ሠፊ ለሆኑ ችግሮቻችን በተናጠልም ሆነ መተክል-አልባና በአጭሩ-ያዬ ጊዚያዊ ስብስብ በመፍጠር የምታገኙት አዎንታዊ ውጤትና የምትሰጡት መፍትኄ እንደማይኖር ተገንዝባችሁ፣ ይኸንን የጋራ ጥረት እውን በማድረጉ ረገድ የሚኖርባችሁን ኃላፊነት እንድትወጡ፤

ስለምትወዷት ኢትዮጵያና ስለምታፈቅሩት ሕዝቧ ስትሉ ይኸንን ጥሪ እንድትቀበሉ ከአደራ ጭምር በአክብሮትና በትኅትና አቀርባለሁ።

የአንድነት ኃይሉ ተሰባስቦ አገሩንና ሕዝቡን ለመታደግ የሚያደርገው ማንኛውም ጥረት ተፈታታኙ ብዙ እንደሆነ ግልጥ ነው። ልንረታውና ልንወጣው የሚገባ ትልቁ ጠላት በየራሣችን ላይ ያደረውና ለረጅም ጊዜ የተሸከምነው ሥነ-ልቦናዊ ጫና ይመስለኛል። ይኸንን በብቃት ከተወጣን ከየአቅጣጫው የሚሰነዘሩ ሌሎች አሉታዊ ዘመቻዎችን ማቸነፉ ቀላል ነው። የኢትዮጵያዊነትና የአንድነት እምነት ቢያንስ-ቢያንስ በአናሣዎች በሚቀነቀን አገር-በታኝና ሕዝብ-ከፋፋይ አስተሣሰብ ሊዋጥም ሆነ ቁጥሩ በጣም የበለጠው የአብዛኛው አገር-ወዳድና ዴሞክራት የአንድነት ወገን ድምፅና ቆራጥነት በቀጣይነት አንሶና ኮስሶ ሊገኝ አይገባም። የእስካሁኑ የተዛባ ሂደት እንዲቀጥል ጨርሶ መፈቀድ አይኖርበትም። የውድ አገራችን ኢትዮጵያና የታላቁ ሕዝቧ ዕድል ዳግም በአናሣ ብልጦች እንዲወሰን መፈቀድ አይኖርበትም። የአገር አንድነት በልመናና በይሉኝታ አይረጋገጥም። ልዩነት አድልዖን፣ ጥላቻንና ትርምስን እንጂ ፍትኅና ርትዕን አያመጣም፣ እኩልነትን አያረጋግጥም፤ በአንድ ምክንያት ይሁን በሌላ ያፈንነውን ድምፅ እናሰማ፣ ሕዝባዊ ኃይላችንና አቅማችን በጥቂቶች ሸብረክ አይበል፣ እራሣችንን እየሰደብን፣ ውድ አገራችንና ታላቁን ሕዝቧንም እያዋረድን መቀጠሉ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በቃ ለማለት ድፍረቱ ይኑረን፣ የኢትዮጵያ አገራዊ አንድነትና ኢትዮጵያዊነት ክብርና ኩራት እንደሆኑ ቀና ብለን በድፍረት እናረጋግጥ እላለሁ። 'ሲበዛም ያነዛል' ነውና ኧረ ይብቃ ጃል!

አመሰግናለሁ።

ኅብረታችን የጋራ ኅልውናችን ዋስትና፣ አንድነታችንም የመልካም ሥርዓት መሠረት ነው!!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!

አያል ሰው ደሴ፡ ጥቅምት፤ ሁለት-ሽህ-አራት ዓ/ም(ሙሉን ሰነድ edhum.net ላይ ማግኘት ይቻላል።)